ምዕራፍ 6

# የፋኖ አሰላለፍ ግምገማ

በአንድ አማራ ንቅናቄ ተዘጋጅቶ የቀረበ ሰነድ
መስከረም 30, 2018

# ማውጫ


የፋኖ አሰላለፍ ግምገማ ........ 2

1. ፋኖ እና የህውኃት ጥምረት የቢሆን ትንተና ........ 4
1.1 ከህወሓት ጋር የሚሰራ ፖለቲካ ........ 4
1.1.1 ሊታመኑ አይችሉም ........ 4
1.1.2 ሰሜናዊ የሚባል ትርክት ........ 5
1.1.3 ወልቃይት እና ራያ ........ 5
1.1.4 ከአማራ ጋር ጥምረት እናደርጋለን በሚል ማስፈራሪያ ........ 5
1.1.5 አማራን መጠቀሚያ ማድረግ ........ 5
1.2 የህወኃት አሰላለፍ ........ 5
1.3 ማሳሰቢያ ........ 6
2. የፋኖ እና ብልፅግና ጥምረት የቢሆን ትንተና፡- ........ 6
2.1 ብልፅግና ሊታመን አይችሉም ........ 6
2.2 የብልፅግና ቀጠናዊ አሰላለፍ ........ 7
2.3. ማሳሰቢያ ........ 7
3. የፋኖ እና ኤርትራ ጥምረት የቢሆን ትንተና፡- ........ 7
3.1 ማሳሰቢያ ........ 8
4. የፋኖ እና ሱዳን ጥምረት የቢሆን ትንተና ........ 8
5. የፋኖ እና ግብፅ ጥምረት የቢሆን ትንተና ........ 9
6. ማጠቃለያ ........ 9

# የፋኖ አሰላለፍ ግምገማ

የአንድ አማራ አደረጃጀት፡ የአማራ ህዝብ ከታሪኩ ከዛሬዉ ብሎም ለወደፊቱ ታማኝ በመሆን ሲታገል ቆይቷል፡ ከዚህም በፊት ብዙ strategic ሰነዶችን በይፋም ይሁን በህቡህ ሲያዘጋጅ የነበረ እና አሁናዊዉ በሆነዉ የወገን ጠላት ብሎም መሀል ሰፋሪ አሰላለፍ ግምገማ አስፈላጊ በመሆኑ ይህ ሰነድ እንዲዘጋጅ ምክንያት ሆኗል።

የአማራ ትግል እስካሁን የመጣበት ሁኔታ ሁለቱን ዋና ጠላቶቹን በሚገባ የለየና ሙሉ ትኩረቱን በነዚህ ጠላቶቹ ላይ አድርጎ የሰራ ነው። እነዚህም የአማራ ህዝብ ታሪካዊ እና ስትራቴጂክ ጠላቶቹም ህወሀት እና ብልፅግና ናቸው።

የመጀመሪያ ጠላቱ ብልፅግና ሲሆን መነሻዉን አማራ ጠል ከሆነዉ የስልሳዎቹ ትዉልድ ስሩን መስርቶ በመነሳቱ በህዝባችን ላይ ሁሉን አቀፍ የህልዉና አደጋ ጥሎበታል። ህዝባችን ይህን ተስፋፊ እና ጨፍጫፊ ሀይል በሁሉም ግንባር በሁለንተናዊ መልኩ እየተዋጋው ይገኛል።

ሁለተኛ የአማራ ጠላት የሆነው ህወሓት ላለፉት 60 አመታት ከአፄ ሃይለስላሴ ጀምሮ እስካሁን ሲችል በጉልበት ሳይችል በሴራ ሲያጠቃን ቆይቷል። የአማራ ህዝብ አሁን ላይ ደግሞ በወልቃይት በኩል ተከዜን እንዳይሻገር ሀይል በማደራጀት ፤ በራያ በኩል ደግሞ በብልፅግና መልካም ፍቃድ የወረረውን መሬት እንዲለቅ ትኩረት ተሰጥቶ እየሰራ ይገኛል። በሌላ በኩል አሁን ላይ በምስራቅ አፍሪካ ጂኦፖለቲክስ አሰላለፍ በፍጥነት እየተቀየረና አዳዲስ የ'Political Alliance እየተፈጠረ ሲሆን "ፅምዶ" የሚባለው የፖለቲካ ጥምረት አንዱ ነው። ይህ ጥምረት የህዝብ ለህዝብ እንጂ ፖለቲካዊ አይደለም የሚል propaganda ቢኖርም በህዉሃት እና በሻቢያ መካከል የተደረገ strategic ጥምረት ነዉ።

በዋናነት ከሻዕቢያ ጋር የፖለቲካጥምረት የፈጠሩት የህወሀት አመራሮች በፖለቲካው ዘርፍ ደብረፂዮን ገብረሚካኤል፣ ሞንጆሪኖ፣ አለም ገብረዋድ ሲሆን በወታደራዊ ዘርፍ ያለውን ደግሞ በተለምዶ "ልዕሊ ኮር" ወይም ግንባር ኣዘዝቲ በመባል የሚታወቁት ከፍተኛ ወታደራዊ አመራሮች ምግበይ ሃይለ፣ ጆን መዲድ፣ ማዕሾ በየነ፣ ተኽላይ አሸብር(ወዲ ኣሸብር) ፣ ፍሳሃ ማንጁስ፣ ግዑሽ ገብረ አብ ፣ ፀጋይ ማርክስ ናቸው። እስካሁን ባለው ሁኔታ የሻዕቢያ ሰወች ወደ መቀሌ ፤ የህወሀት ሰወች ወደ ኢዲሃሎ(አስመራ) መመላለሳቸው እና በትግራይ እገላ እና በኤርትራ በገለው ፈርዳ እንዲሁም በትግራይ ዛላምበሳ እና በኤርትራ ሰነአፈ፣ አካለ ጉዛይ፣ እንዳ ኣርበአተ እና ሰራዬ መስመር ያለው ድንበር ክፍት እንዲሆን መደረጉ የሚጠቁመን ነገር አለ።

ይህ መስመር ከፍተኛ የትጥቅ እንቅስቃሴ ያለበት ነዉ። በሌላ በኩል ደግሞ የህወሀት ሰራዊት ደቡብ ግንባር አዛዥ በሆነው በጀነራል ዮሀንስ(ጆን መዲድ) የሚመራ የህወሀት ቡድን ከአማራ ፋኖ ጋር ቁጥር 2 ፅምዶ ለመፍጠር በራያ መሆኒ፣ በዋጃ እንዲሁም በስልክ ከአማራ ፋኖ አንዳድ አመራሮች ጋር ግንኙነት መጀመራቸው የሚታወቅ ነዉ።
እነዚህ ከህወሓት ጋር ለመጣመር እንቅስቃሴ እያደረጉ የሚገኙት አንዳድ የፋኖ  አመራሮች ስትራቴጂክሊ ማሰብ የማይችሉ ማለትም

- ራዕይ የሌላቸው
- የሚመጣውን ሁኔታ መተንተን የማይችሉ
- አሁን ያለውን አሰላለፍ በቅጡ የማይገነዘቡ
- በትክክለኛው ሰዓት ትክክለኛ ውሳኔ ማሳለፍ የማይችሉ
- አጀንዳቸው ቅቡል እንዲሆን የማይሰሩ እና ኢጋር ከማብዛት ይልቅ ሌሎች የፋኖ ድርጅቶችን ለማጥፋት ከጠላት በላይ እንቅልፍ አጥተው የሚሰሩ ብሎም ወዳጅ እና ጠላትን በሚገባ የማይለዩ ናቸው።

ኢህዴን/ብአዴን ጎበዝ ተዋጊዎች  እንጂ ስትራቴጂክ የፖለቲካ አመራር ስላልነበረው በደርግ ውድቀት ማግስት የአማራ ህዝብ ላይ የተሰራውን ሸፍጥ ማስቆምም ሆነ ፖለቲካሊ መገዳደር የተሳነው ተላላኪ ድርጅት እንደሆነ ሁሉ ዛሬም የህወሃት አመራሮች ከአማራ ፋኖ ጋር ያለዉን ጥምረት የሚያዩት ከ 40 አመታት በኋላ "እንዳሻቸው የሚዘውሯቸውን አቅመ ቢስ አመራሮች እና ብዛት ያለው ጀግና ተዋጊ" ተጠቅመው የሚያገኙትን ስልጣን፣ የሚቀሙትን ርስት እና ህዝባችን ዳግም እንዳይነሳ የሚሰሩበትን የማፍረስ ፖለቲካ ነው።

አሁን ላይ በብልፅግን ትንኮሳ ምክንያት ከፋኖ ጋር ለመስራት ህወሀት፣ ኤርትራ ፣ ሱዳን ፣ ግብፅ ፍላጎታቸውን ያሳዩ ሲሆን የብልፅግና ሀይል ደግሞ ፋኖን ዳግም ለመጠቀም strategy/እቅድ ነድፎ እየሰራ ይገኛል።

## 1. ፋኖ እና የህውኃት ጥምረት የቢሆን ትንተና :-

ህወሀት ማለት ከጥንስሱ የአማራን ህዝብ በማኒፌስቶ ጠላት አድርጎ የተነሳ፣ የአማራን ህዝብ በጥምረት ሽፋን ተዋጊ አድርጎ መንግስት ከሆነ በኋላም "ነፍጠኛ እና ሽፍታ ማፅዳት በሚል Genocidal code የአማራ ህዝብ ላይ ጦርነት ያወጀ ፣ በሽግግር መንግስቱ አማራ እንዳይወከል ያደረገ፣ የአማራ ርስቶች ቀምቶ የወሰደና ብቸኛ ተጠያቂ እንዳይሆን ለሌሎችም ያደለ ሲሆን ለአብነት ያህል መተከል፣ ራያ እና ወልቃይት ብቻ 45,987.79 sq.km የሚሸፍን ነዉ ፣ ይህ መሬት አሁን አማራ ክልል ተብሎ የተካለለውንን 29.7% ወይም ⅓'ኛ ይሸፍናል። ይህ እንግዲህ ለሱዳን የሰጡትን አልፋሽጋ እና ወደ ኦሮምያ የተካለለውን የሸዋ የአማራ ርስት ሳይጨምር ነው። በቅርቡ የተካሄደውን የሰሜኑን ጦርነት ሳይጨምር በሚሊዮን አማሮች ላይ ግድያ፣ ማፈናቀል፣ እስር ፣ መሰወር ብሎም ለስደት የዳረገ ድርጅት ነዉ። በፓርላማ የታመነ 2.5 ሚሊዮን አማራ ህዝብ ቁጥር በመቀነስ የአማራ ህዝብ ከሁሉም ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ ብሎም ኢኮኖሚያዊ ማሳነሶችን ከመፈፀም ባለፈ ፣ ሌሎች ብሄሮች አማራን ከሀረርጌ እስከ ጉራፈርዳ ፤ ከመተከል እስከ ወለጋ የሚገድሉበትን ትርክት ያዋለደ እንዲሁም የጨቋኝ ተጨቋኝ ትርክት ከመፍጠር ባለፈ የተለያዩ የታጠቁ ሀይሎች በመፍጠር እና ቀጥተኛ ትዕዛዝ በመስጠት ህዝባችንን የጨፈጨፈ ድርጅት ነዉ። ይህ ድርጅት ጠላት ከመሆኑ ባሻገር የፅምዶ አጀንዳ ከተነሳ ወዲህ ደግሞ ከአፄ ዘረ ያዕቆብ ጀምሮ ጄኖሳይድ ተፈፅሞብኛል እንዲሁም የተስፋፊነት ፍላጎቱ ከአላውሃ ምላሽ እስከ ሊማሊሞ በመለጠጥ እየተንቀሳቀሰ የሚገኝ ነዉ። ለአብነትም መላዉ ራያ ብሎም ከ ጠለምት ወደ ወልቃይት የሚወስደዉ መንገድ ላይ ያሉ ለህዉሃት አይገዙም ተብለዉ የተፈረጁ የፋኖ አመራሮች ላይ የማደኛ አዋጅ አዉጆ ፋኖ ፋኖን አጥፍቶ መንገድ እንዲከፍትላቸዉ የትጥቅ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል። ይህንንም በትግራይ በቅርቡ በተካሄደዉ ብሄራዊ ስብሰባ ላይ በግልፅ በመደምደሚያ በመግለጫ አስቀምጦታል።

### 1.1 ከህወሓት ጋር የሚሰራ ፖለቲካ

#### *1.1.1 ሊታመኑ አይችሉም*

- ደርግን ከአማራ ህዝብ ጋር አብረው ከታገሉ በኋላ አማራን በሽግግር መንግስቱ እንዳይወከል አድርገዋል።

- ደርግን ከኦነግ ጋር አብረው ከታገሉ በኋላ ስልጣን በምርጫ ነው የሚያዘው በማለት የኦነግን ጦር በ'8 ካምፕ ከጠረነፉ በኋላ ቃላቸውን በማጠፍ መጋቢት ወር 1984 በካምፕ የጠረነፉትን የኦነግ ጦር ደምስሰዋል።
- በቅርቡ በተደረገው የሰሜኑ ጦርነት ላይ ህወሓት ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር ፣ከአገው ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ እና ከጋምቤላ ሀይሎች ጋር ጥምረት የፈጠሩ ቢሆንም ያለ እነሱ እውቅና ከብልፅግና ጋር ፕሪቶሪያ ላይ ተፈራርመዋል።

### *1.1.2 ሰሜናዊ የሚባል ትርክት*

ሰሜናዊነት የሚባል የጋራ ማንነት በሰሜኑ ኢትዮጵያ ታሪክ ተፈጥሮ አያውቅም። ይህን ሰሜናዊ የሚባል የጋራ ማንነት ለመፍጠርም የሚያበቃ የታሪክ፣ የቋንቋ፣ የባህል፣ የእሴት፣ እና የአስተሳሰብ አንድነት አልነበረም ዛሬም የለም። በአጭሩ ሰሜናዊነት ማለት በራስ ካለመተማመን የመጣ የጥገኝነት መንፈስ ነው።

### *1.1.3 ወልቃይት እና ራያ*

የህዉሃት ሀይል በአማራዉ እርዳታ እነዚህን አካባቢዎች ከተቆጣጠረ በኃላ ህዝቡን አስፍሮ ወደ referendum በመግባት ክልሉን የማስፋት አልያም ኢትዮጵያን balkanize አድርጎ Republic ይሆናል።

### *1.1.4 ከአማራ ጋር ጥምረት እናደርጋለን በሚል ማስፈራሪያ*

ከአማራ ጋር ጥምረት እናደርጋለን በሚል ማስፈራሪያ ብልፅግናናን አስገድደው የራሳቸውን ፍላጎት ማስፈፀም ይህም የተፈናቀሉ በሚል ሚሊዮኖችን ወደ ወልቃይት እና ራያ ካሰፈሩ በኃላ የራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ የሚያነሱ ይሆናል።

### *1.1.5 አማራን መጠቀሚያ ማድረግ*

ከተቻለ በአማራ እገዛ የ'1983 አይነት የስርአት ለውጥ ማምጣት በመጣዉም ለዉጥ አድራጊ ፈጣሪ መሆን።

## **1.2 የህወኃት አሰላለፍ**

አሁን ባለው ሁኔታ የትግራይ ፖለቲካ አሰላለፍ በ 2 የተከፈለ ሲሆን በደብረፂዮን የሚመራው "ህወሓት" እና በጌታቸው ረዳ የሚመራው "ስምረት ትግራይ" ዋና ተጠቃሽ ናቸው። ሁለቱም የራሳቸው ታጣቂ ሀይል ያላቸው ሲሆን ህወሀት በተንቤን "አግበ" ሰራዊቱን እያደራጀ ሲሆን "ስምረት ትግራይ" በበኩሉ በአፋር "ሃራ መሬት" በሚል ሰራዊቱን እያደራጀ ይገኛል።

እነዚህ ሁለት ሀይሎች በትግራይ ያላቸው ማህበራዊ መሰረትም የተለያየ ሲሆን የህውሀት አመራሮች በዋናነት ከኤርትራ በቅርብ ርቀት የሚገኙት የአክሱም፣ ሽሬ እና አድዋ(አሽአ) አከባቢወች ሲሆኑ ጥምረታቸውንም ከኤርትራ ጋር አድርገዋል። የወልቃይት ኮሪደር መዘጋቱን ተከትሎና በሱዳን የእርስበርስ ጦርነት ምክንያት ከጀነራል አልቡርሀን ጋር የነበራቸው ጥምረት ተቋርጧል።

በሌላ በኩል በጌታቸው የሚመራው የትግራይ ሀይሎች ማህበራዊ መሰረታቸውን በእንደርታ፣ ማይጨው ራያ እና ተንቤን በማድረግ ጥምረታቸውን ከፌደራል መንግስቱ ጋር ያደረጉ ሲሆን በአለም አቀፉ ዲፕሎማሲ መድረክም ላይ ከህወሓት የተሻለ ተቀባይነት አላቸው።

**1.3 ማሳሰቢያ**

ህዉሃት ባላት አለማቀፋዊ የዲፕሎማሲ አቅም፣ የፖለቲካ እና ወታደራዊ ጥንካሬ ምክንያት ከአማራ ፋኖ ጋር ጥምረት ቢፈጠር የአማራ ፋኖ ተራ የእግረኛ ተዋጊ ከመሆን በዘለለ ቁልፍ ተዋናይ ሆኖ መዉጣት አይችልም፣ የአማራ ፋኖን ከተጠቀመች በኃላ ፣ አማራዉን እርስበርሱ በማዋጋት ህዝቡን አዳከመዉ ክልሉን አፍርሰዉ ከቻሉ ለንዑስ ብሄሮች አሳልፈዉ በመስጠት ፣ ከኦሮሚያ ሀይሎች ጋር በመሆን ከጦርነት የተረፈዉን ከበባ ዉስጥ በመከተት ቀጥቅጠዉ ለመግዛት የሚንቀሳቀሱ ይሆናል።

## 2. የፋኖ እና ብልፅግና ጥምረት የቢሆን ትንተና:-

### 2.1 ብልፅግና ሊታመን አይችሉም

- ኦህዴድ/ብልፅግና ኦሮማራ በሚባል ያልተቀደሰ ጋብቻ ወደ ስልጣን ከወጣ በኋላ አማራን confuse and convince አደረግናቸው ያለ የማይታመን ሀይል ነው
- በሰሜኑ ጦርነት የአማራ ልዩ ሀይልን ድረስልኝ ብሎ በአማራ ደም ስልጣኑን ካፀና በኋላ የአማራ ልዩ ሀይልን ለማፍረስ የሰራ ሀይል ነው።
- በሰሜኑ ጦርነት ወቅት ደጀን ያለውን የአማራ ህዝብ ላይ በአየር እና በምድር ጦር አሰማርቶ ጄኖሳይድ እየፈፀመ ያለ ነው።
- በጦርነቱ ወቅት የአማራ ነው ሲለው የነበረውን የራያን ህዝብ እና መሬት ሆነ ብሎ በጌታቸዉ ረዳ ለሚመራዉ መንግስት ማጠናከሪያ እንዲሆን በስጦታ መልክ እንዲወረር ያደረገ ነዉ።

- በምንጃር ወረዳ አሞራ ቤትን ጨምሮ የአማራን መሬቶች በሀይል የመያዝ ፍላጎት ያለው ስብስብ ነው። በቅርቡ የተደረገው የእሬቻ ባዛርና ሲምፖዚየም ሳይቀር ወሎን የኦሮምያ አካል አድርጎ የሚያሳይ ካርታ ለእይታ ያቀረበ ተስፋፊ genocidal culture ያለዉ ነዉ።
- አማራን በትርክት እና በውስጣዊ ፖለቲካ የማተራመስ እና ማህበራዊ እረፍት እንዳያገኝ የሚሰራ ስብስብ ነዉ።
- የዚህ ድርጅት ዋና አላማ አማራን ማፍረስ፣ ፋኖን ይዞ ኤርትራ ላይ መዝመት፣ የአማራን መሬት የወታደር እና ሎጂስቲክስ ማከማቻ ከማድረግ ያለፈ ማሰብ የማይችል ነው፡ በሚደረጉ ጦርነቶች ሁሉ አማራን ከፊት አሰልፎ እንዲደቅ ማድረግ ነዉ።

**2.2 የብልፅግና ቀጠናዊ አሰላለፍ**

ብልፅግና በምስራቅ አፍሪካ ቀጠና ምንም አይነት ስትራቴጂክ የፖለቲካ አጋር የሌለው ሲሆን የኢትዮጵያን የፖለቲካ አሰላለፍም ከምስራቅ ወደ ምዕራብ በማዞር የአሰላለፍ ለውጥ ያደረገ ቢሆንም ፣ በምዕራቡ ዘንድ እምነት ያልተጣለበትና ከሁለት ያጣ ሆኗል። ለአባይ ግድብ ምረቃ እንኳ ከሁለቱም በኩል ጥሪ የተደረገላቸው ሀገራት ያልተገኙ ሲሆን ፣ አሁን ላይ በትንሿ UAE ዶላር የሚዘወር ብቻ ሆኗል።

**2.3. ማሳሰቢያ**

በብልፅግና ተደራጅቶ ከአሰብ በተያያዘ ለዚህ ሀሳብ ያልተሰለፈን በጠላትነት ብሎም በባንዳነት አማራን ለመፈረጅ የተደራጀ የኪነት ብሎም የእምነት ጎራ ልየታ በማድረግ በስም መዝግቦ መጠበቅ እና አስፈላጊዉን የ propaganda እና የተለያዩ  ዘመቻዎች ለማድረግ በተጠንቀቅ መቆም ያስፈልጋል። ከብልፅግና ጋር የሚደረግ ማንኛዉም ጥምረት መጨረሻዉ ወደ አሰብ ለሚደረገዉ ዘመቻ ተራ የእግረኛ ተዋጊ መሆን እና በጦርነቱ ማግስት ከዚህ በፊት እንደተደረገዉ ትጥቅ ማስፈታትና የዘር ጭፍጨፋ አዙሪት ዉስጥ የምንገባ ይሆናል።

## 3. የፋኖ እና ኤርትራ ጥምረት የቢሆን ትንተና:-

ኤርትራ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከብልፅግና ያለባትን ቀጥተኛ የወረራ ስጋት እንዲሁም ፤ ብልፅግና በዋናነት ከኤርትራ አካለጉዛይ የተሰባሰቡትን ብርጌድ ንሓምዱ እና ከአፋር ብሄረሰብ የተሰባሰቡትን የቀይ ባህር አፋሮች ንቅናቄን በማስታጠቅ፣ ፖለቲካዊ ድጋፍ እና ስልጠና ከሚሰጣቸው አካላት የተጋረጠባትን ስጋት ለመቀልበስ ከግብፅ፣ ሳውዲ አረቢያ፣ ሶማልያ እና ትግራይ ጋር በግልፅ መስራት የጀመረች ሲሆን በሌላ በኩል እንደ ፋኖ ካሉ ሀይሎች ጋር የመስራት ፍላጎት እንዳላት የሚታወቅ ነው። ብልፅግናም ቢሆን

በቅርቡ ለ UN ያስገባው ኤርትራን የመውረር ዛቻ የነገሩን ጡዘት የሚያመላክት ሲሆን ይህን ሁኔታ አርቀው ማሰብ በሚችሉ የፋኖ አመራሮች ታይቶ አቋም መያዝ ይገባል።

**3.1 ማሳሰቢያ**

ኤርትራ በሀያላን ምዕራባዊ ሀገራት የጠላትነት መዝገብ ዉስጥ የተቀመጠች ስለሆነች: ከኤርትራ ጋር ፊት ለፊት መስራት በዲፕሎማሲ በኩል ፋኖ ላይ ጫና ሊያመጣ ይችላል፣ ከኤርትራ ጋር ለመስራት ሲታሰብ ይህንን ኪሳራ ከግምት ያስገባ መሆን ይኖርበታል።

የኤርትራ ሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ አቅም እጅግ ደካማ በመሆኑ የተራዘመ ጦርነት ቢደረግ፡ ፈጣን የሆነ የቁሳቁስ እርዳታ ማቅረብ አትችልም። ከዚህ ሀይል ጋር ተጣምሮ ለመስራት ሲታሰብ የጊዜ አፋጣኝነት ሁሌም ሊታወስ የሚገባ ነዉ።

በአፋር፣ በእምነት ብሎም በብሄር ምክንያት የተዳፈነ የፖለቲካ እሳት በመኖሩ ሻቢያ/ህግደፍ ሸርተት ካለ ልንገምተዉ የማንችለዉ የኤርትራ ዉስጣዊ መናጥ ሊፈጠር ይችላል። የውስጣዊው ሽኩቻ ፋኖ ላይ ጫና ሊያመጣ ይችላል።

ከላይ የተዘረዘሩትን ያማከለ ከኤርትራ ጋር ያለ አጃቢ በብቸኝነት የሚደረግና አስፈላጊ እና አስገዳጅ ሆኖ እስኪገኝ ድረስ በህቡዕ ብቻ መስራት ያስፈልጋል ።

## 4. የፋኖ እና ሱዳን ጥምረት የቢሆን ትንተና

ሱዳን ላለፉት 2 አመታት በጀነራል አልቡርሃን እና ሄሚቲ በሚመሩ ሀይሎች የውግያ ማዕከል ሆናለች። አሁን ላይ አልቡርሀን ካርቱምን ዋና መቀመጫ አድርጎ መንግስትነትን ያፀና ቢሆንም ሄሚቲ በበኩሉ ደግሞ ኒያላን ዋና መቀመጫው አድርጎ መንግስትነትን አውጀው ይገኛሉ።

በሱዳን አሁንም የህዉሃት ሰራዊት እንደነ ፍሬዘር ኪሮስ ባሉ የኮማንዶ አሰልጣኞች እና ከመስመር መኮንኖች እንደ አርሚ 70 ያሉ በሀይል እየተደራጁ በመሆኑ ፣ በሱዳን ድንበር ከ አልቡርን ሀይሎች ጋር በመጣመር በምዕራብ አማራ በኩል የማያቋርጥ ጥቃት በመሰንዘር በጠለምት፣ ቅዱስ ሚካዔል አድርጎ ወደ ብልአምባ ለመወርወር የተዘጋጀዉ የህዉሃት ሀይል ጋር ወልቃይትን ከበባ ዉስጥ ሊከት ይችላል፡ ይህም

ከሸሬ አፈንግጫለሁ ብሎ በላይኛዉ ጠለምት እየተደራጀ ያለዉ የህዉሃት ሻለቃ ጦርነቱ የሚለኮስ ይሆናል። ለዚህም ከደባርቅ፣ ደምብያ ብሎም ጎንደር ከተማ ዙሪያ ያሉ ህዉሃት ጠል የ ፋኖ አደረጃጀቶች ላይ በእጅ አዙር ጦርነት ከፍቶ ይገኛል።
እነዚህ ሁለት ሀይሎች ከአማራ ፖለቲካ አንፃር ስንቃኛቸው እነ አልቡርሀን የምዕራብ አማራን አልፋሽቃን መሬት የመውረር ፍላጎት ያለው ሲሆን ሄሚቲ ግን ከአልቡርሀን በተቃራኒ የመስፋፋት ፍላጎት የሌለው ሆኖ ይታያል። በሌላ በኩል አልቡርሃን አብይ አህመድን የሚጠላ ሲሆን ሄሚቲ ግን በ UAE አማካኝነት ለአብይ የቅርብ ወዳጅ ናቸው። የሱዳን ፖለቲካ እንደ ዳርፉር ያሉ እንዲሁም በዋናነት ለአማራ ህዝብ ጎረቤት የሆኑት የብሉናይል እና ደቡብ ኮርዶፋን ያሉ ህዝቦች የመገንጠል እንቅስቃሴ የሚያደርጉበትና አለማቀፍ ተዋንያን የሚሳተፉበት እንደመሆኑ በሳል በሆኑ የፋኖ አመራሮች ተገምግሞ አቋም ሊያዝበት ይገባል።

## 5. የፋኖ እና ግብፅ ጥምረት የቢሆን ትንተና

የግብፅ ህዝብ በአባይ /ናይል ዉሃ ላይ የተመሰረተ ህይወት ያለዉ በመሆኑ በዚ ዉሃ ጉዳይ ዘለዓለም መታገል ካለበት ዘላለም ሊታገል ይችላል፣ ከዚህም በኃላ ጫናዉን እያጠነከሩ የሚሄዱ ይሆናል። ከነዚህም አንዱ በኢትዮጵያ ካሉ ሀይሎች ጋር በመስራት አገሪቷን ማዳከም፣ ይህ የማይሆን ከሆነ ብልፅግናን ጥሎ ስልጣን ከሚይዘዉ ሀይል ጋር በካምፕ ዴቪድ ስምምነት ማግስት ከ እስራዔል እንዳደረጉት፣ እጅና ጓንት ሆነዉ በመስራት ላለመግባባታችን የ engineering መፍትሄ ፈልጎ ከ suez canal ጀምሮ እስከ somalia እና ፣ ከ አማራ  እስከ ሱዳን ባለዉ ጠንካራ የ ወታደራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀጠና በመፍጠር ፣ ከመካከለኛዉ ምስራቅ እስከ አፍሪካ ቀንድ ቁጥጥር ማድረግ ይሆናል። ለዚህም በ ምዕራባዉያን  ሀገራት ብሎም በእስራዔል የምትደገፍ ይሆናል። ለዚህም የአማራ ፋኖ በምስራቅ አፍሪካ ካሉ ሀይሎች ትልቅ የስበት ሀይል ሆኖ ይገኛል።

## 6. ማጠቃለያ

እንደ ማጠቃለያ የአማራ ፋኖ በአሁኑ ሰዓት፣ የኤርትራ፣ የህዉሃት፣ የግብፅ ፣ የብልፅግና ብሎም የመላዉ ኢትዮጵያዉያን የህልዉና ጉዳይ ከሚወስኑ ሀይሎች ቀዳሚዉን የሚይዝ መሆኑን፣ በማወቅ አሁን ባለዉ አሰላለፍ አማራ ሳያሸንፍ ሌሎች የሚያሸንፉት በአማራ መቃብር ላይ መሆኑን ተረድቶ፤ በዚህም ታሪካዊ መስቀለኛ መንገድ የቆመ በመሆኑ ቆም ብሎ አማራ አለዉ የሚለዉን ዕዉቀት በሙሉ ሰብስቦ መክሮ ከተዘዋሪ ወደ ዘዋሪነት በፍጥነት በመቀየር የአባቶቹ ልጆች መሆኑን ማሳየት ይኖርበታል።

እኛም የአባቶቻችን ልጆች ነን፣ አማራ ያሸንፋል!

***ይህ ሰነድ ለመላዉ አማራ ይፋዊ በሆነ መልኩ የዉይይት መክፈቻ እንዲሆን ታስቦ በአንድ አማራ ንቅናቄ ተዘጋጅቷል።

ይህን ጥራዝ ተከትሎ ከሚወጣው (ምዕራፍ 7) ሰነድ ውጪ ሌሎች ጥራዞችን የአንድ አማራ ንቅናቄ የማያውቃቸው መሆናቸውን አንባቢው እንዲረዳ እንመክራለን። በዚህ ጥራዝ ማህበረሰቡ እንዲሰበሰብ ታስቦ ፍፁም ይፋዊ በሆነ መንገድ በአንድ አማራ ንቅናቄ የማህበራዊ ትስስር ገፆች አዲለቀቅ ተደርጓል።


አንድ አማራ ንቅናቄ

ONE AMHARA

Email: one_amhara@mail.com

Twitter: @one__amhara

YouTube: አንድ አማራ ሚድያ ( One Amhara Media)